በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ




# ከኦገስት 21-31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

# ግምገማ እንዲሁም

# ከሴፕቴምበር 1-10፣ 11-10/2026 የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ ትንበያ

# እና ምክረ ሃሳብ


ሴፕቴምበር 2026

አዲስ አበባ

## 1. እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በ51 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1) ፡፡


በተጨማሪም በምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40-133 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል አደዋ 45.6፣ አንገር ጉትን 40፣ ቢላምቢሎ 40፣ ቦሬ 43፣ ቡለን 65፣ ድንግላ 45.7፣ ደብር ሲና 47.2፣ ጊምቢ 82.4፣ ጎንደር 51፣ ሊሙገነት 61.7፣ ማይጨዉ 79.5፣ ማጀቴ 42.5፣ ማሻ 133፣ ሮቢት 42.2፣ ሽሬ 40.6፣ ጽጺቃ 46.8 ይገኙበታል ፡፡





ምስል1:ከኦገስት 21 እስከ 31/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ አዲስ አበባ ላይ ከ31-210 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ሁሉም ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኙዋክ፣ መዥንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ አዲስ አበባ በአብዛኛ መደበኛ እና በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው የአፈር ዉስጥ እርጥበት ሁኔታ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የረጅም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለፍራፍሬዎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡ ፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለይም በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ለሚገኙት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የመጠጥ ውሃ እና የግጦሽ ሳር አቅርቦት ጠቀሜታ ነበረዉ፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በተለይም በዋግህመራ ዞን ከነበረው በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በሰብሎች ላይ ጉዳት አድረሷል፡፡ (ካርታ 4)።

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የኦገስት ሶስተኛው አስር ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ በላይኛውና መካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት የላይኛው ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ አዋሽ፣ የተከዜ፣ መረብ ጋሽ እንዲሁም የአፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ በጣም ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት መሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅዖ የነበረው ሲሆን በአንጻሩ ግን በከፊል የአፋር ደናክል፣ ኦጋዴን፣ አይሻ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ እንዲሁም የታችኛው ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች በደረቅ እርጥበት ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 5)።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2026
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2026
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ ሴፕቴምበር የክረምት የመጨረሻ ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ ከሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየቀነሰ የሚሄድ ሲሆን፤ በአንጻሩ ለረጅም ጊዜ ደረቅ ሆነው የሰነበቱት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን ማግኘት ይጀምራሉ። በዚህም መሠረት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ከ100-300 ሚ.ሜ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም ከ12-23 ለሚደርሱት ቀናት ያህል ዝናብ ይኖራል። በሌላ በኩል በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት እየቀነሰ የሚሄድ በመሆኑ ከ3-15 ቀናት ያህል ከ20-200 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ይኖራል። የደቡብና የደቡብ ምስራቅ ስፍራዎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የሚጨምር በመሆኑ 30-100 ሚ.ሜ ከ3-12 ቀናት ይደርሳል፡፡


### 2.1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በመጪዎቹ የሴፕቴምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች እየተስፋፉና እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው አህዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም፣ በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ መካከለኛው እና ምዕራብ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በሚቀጥሉት አስር ቀናት ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከመካከለኛ እስከ ከባድ (ከ11-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 1-10, 2026 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 1-10, 2026 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ሸገር ሲቲ እና ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ እና የምዕራብ ጉጂ ዞን | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የምዕራብ፣ መካከለኛው፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም እና የአዊ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ዋግህምራ፣ የደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካካለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ በላይ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ መካካለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ በላይ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካካለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ በላይ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከቀላል እስከ መካካለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ በላይ) |

| | | |
|---|---|---|
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅ፣ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካካለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ በላይ) |
| አፋር | የአዉሲ፣ ማሂ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | አብዛኛው የክልሉ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ጎፋ እና ጌድዮ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት የክረምት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች እየተዳከሙ የሚሄዱበትና ከዚህም ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት በጎላ መልኩ እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ በሌላ በኩል የክረምት የዝናብ ድንበር (ITCZ) ወደ ምዕራባዊው አጋማሽና ወደ ደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍሎች ስለሚያፈገፍግ ዝናቡ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታም የደቡብ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሁለተኛውን የዝናብ ወቅታቸውን ቀስ በቀስ ማግኘት ይጀምራሉ፡፡

በሚቀጥሉት የሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም፤ በሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ እንዲሁም መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀን ወደ ቀን የደመና ሽፋን እየጨመረ እንደሚሄድ ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

## 2.4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የሴፕቴምበር የመጀመሪያዉ አስር ቀናት በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገራችን አካባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል። በመሆኑም የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ ለመጠቀምና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የሚያስችል ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከወዲሁ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 2)፡፡

## 2.5 እ.አ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የሴፕቴምበር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሃገራችን ተፋሰሶች ላይ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል (ሠንጠረዥ 3) ፡፡

Ethiopian Meteorology Institute

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ እንዲሁም አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች | | | |
| --- | --- | --- | --- |
| **ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የተሰጠ ምክረ ሃሳብ** |
| ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፤ ጅማ ፣ የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም ዞኖች ፣ አዊ ፣ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ➢ ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት እና ፍሬ ለማፍራት<br>➢ ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል<br>➢ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ለማጎልበት<br>➢ ለቋሚ ተክሎች እድገት እና ለከተማ ግብርና እንዲሁም ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ እና ለአረንጓዴ አሻራ መረሃ ግብሮች | ➢ የእርጥበት መብዛት እና ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውኃ በሰብሎች ላይ መተኛት<br>➢ ውሃገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ሰብሎች ላይ የአፈር መታጠብ<br>➢ የአረም መስፋፋት<br>➢ የሰብል በሽታና ተባይ መከሰት<br>➢ የበረዶ ክስተት | ➢ ተዳፋታማ ማሳዎች ላይ የተዘጉ የማፋሰሻና የማንጣፈፊያ ቦዮችን ማስተካከል<br>➢ የሰብል በሽታንና አረምን አስቀድሞ መከላከል፤<br>➢ የአፈር መሸርሸር መከላከል ስራዎችን በስፋት መስራት<br>➢ የመሬት መንሸራተት ተጋላጭነትን መቀነስ<br>➢ እርጥበት አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>➢ አርሶ አደሮች የማሳ ጉብኝት በየጊዜው ማድረግ<br>➢ አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር |

| ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ሸገር ሲቲ ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ ፣ ምዕራብ ጉጂ ፣ ዋግህምራ፣ ደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ፣የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ፣ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ ፣ ሐረሪ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅ፣ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች ፣ አዉሲ፣ ማሂ፣ ሀሪ ፣ ጋቢ ፣ የሲዳማ አብዛኛው የክልሉ ዞኖች፣ ወላይታ፣ጎፋ ፣ ጌድዮ ፣ ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ➢ ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት እና ፍሬ ለማፍራት<br>➢ የአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ፣ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል<br>➢ የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማጠራቀም | ➢ የዝናብ መቆራረጥና ደረቅ ሰሞናት መኖር<br>➢ የትነት መጠን መጨመር፤<br>➢ የሰብል በሽታ መከሰት፤<br>➢ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት ዝቅተኛ መሆንና<br>➢ ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን | ➢ የሚገኘዉን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም<br>➢ የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>➢ የአፈር ውስጥ የትነት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤<br>➢ ለእንስሳት የግጦሽ ሣርን በአግባቡ መጠቀምና መጠበቅ፤ |

Ethiopian Meteorology Institute

## ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| አብዛኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ በላኛውና መካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ በላኛዉ የገናሌ ዳዋ | • የገጸ ምድርና የወንዞች ውሃ መጠን መጨመር። <br>• የከርሰ ምድር ውሃ ይዘት መሻሻል። <br>• ለመስኖና ለኃይል ማመንጫ የሚውሉ ግድቦች የውሃ ክምችት መጨመር። <br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል። <br>• የውሃ ኃይል ምርታማነት መጨመርና መሻሻል። <br>• በደረቅ ወቅት የወንዞች መሠረታዊ ፍሰት መጠናከር። <br>የውሃ ሀብት ተደራሽነትና የአካባቢ ኢኮኖሚ መሻሻል። | • የደለል ስጋት መኖር <br>• የውሃ ማፋሰሻ ቱቦዎች በቆሻሻ መዘጋት | • የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም <br>• የመጠጥ ውሃን አክሞ መጠቀም <br>• ትንበያዎችንና ምክረ ሀሳቦችን በየጊዜው መከታተል <br>• የፍሳሽ መውረጃ ቦዮችን ማፅዳት <br>• የጎርፍ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት |
| **ከቀላል እስከ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| የታችኛው አዋሽ፣ የላይኛው ዋቢ ሸበሌና ተከዜ፣ መረብ፣ | የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል <br>• የጎርፍም ሆነ የደለል ስጋት መቀነስ | • ከፍተኛ ትነት <br>• ዝቅተኛ የውኃ ፍሰት <br>• እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች መጠነኛ የውሃ እጥረት | • የሚገኘውን የዝናብ ውኃ አክሞ መጠቀም <br>• ወራጅ የዝናብ ውኃን ማሰባሰብና ማጠራቀምከቤት ጣራ ላይ ውኃ የመሰባባሰብና ማጠራቀም ስራዎች <br>የአየር ሁኔታ መረጃን በቅርበት መከታተል |
| **ደረቅ የአየር ሁኔታ** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| ኦጋዴን፣ የመካከለኛውና ታችኛው ዋቤ ሸበሌ፣ አፋር ደናክል፣ አይሻ፣ እንዲሁም የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች | • የጎርፍም ሆነ የደለል ስጋት አለመኖር፣ | • የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት መቀነስ <br>• የትነት መጠን መጨመር | • የሚገኘውን ውኃ በቁጠባና በአግባቡ መጠቀም <br>• የገጸ ምድር የውኃ ሀብትን በአግባቡ መያዝ |